# ዙር 2 የግል አገልግሎቶች ዝርዝር ተግባራት

## የሠራተኞች ጤናና ደህንነት

ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ከባቢያዉ ሁኔታ መቅረቡን ማረጋጋጥና ሠራተኞችን ስለ አመላካቾች፣ የህመም ምልክቶች ና ከCOVID-19 ህመም ጋር የተያያዙ የስጋት ምክንያቶች፣ እንዴት የኮሮናቫይረስ ስርጭትን ሥራ ቦታ መከላከል እንደሚቻል ማህበራዊ ርቀትን ሥራ ቦታ ላይ ለማቋቋም የተወሰዱ እርምጃዎችን፣ በየግዜዉ እጅ መታጠብን ና ሌሎች ጥንቃቄዎችን ጨምሮ ማስተማር። የማህበረሰብ መመሪያዎችን ከ30 ቋንቋዎች በላይ ለማግኘት www.kingcounty.gov/covid ይጎብኙ።




በሁሉም ግዜያት በሠራተኞችና ደንበኞች መካካል በትንሹ የ6 ጫማ ርቀት ይጠብቁ።



ለሠራተኞች ነጻ የፊት መሸፈኛና ተጠቅመዉ የሚጥሉት ጓንት ያቅርቡ። ለራስዎና ሠራተኞችዎ የፊት መሸፈኛዎችን ለማግኘት seattle.gov/mayor/covid-19/seattle-protects ይጎብኙ።



በየግዜዉ እጅ መታጠብን ያረጋግጡ።



ለያንዳንዱ ሽፍት ብቸኛዉ ሚናዉ የሠራተኛ ጤናና ደህንነት እና ባግባቡ የጽዳት፣ የንጽህና ና የመለየት አሰራሮች መከተላቸዉ ማረጋጋጥ የሆነ የCOVID-19 ተቆጣጣሪ ይመድቡ።




እያንዳንዱ ሠራተኛ ለሥራ እንደመጣ ወዲያዉ ሙቀት ይለኩና ሠራተኞችን የCOVID-19 ምልክቶች እንዳለባቸዉ ይለዩ። ሠራተኛ ምልክቶችን ካሳየ ወዲያዉ ወደ ቤት ይላኳቸዉና ያ ሠራተኛ የነካቸዉን ሥፍራዎች/ገጾች በደንብ ያጽዱ።




የ COVID-19 ደህንነት መረጃና መስፈርቶች በምታይ ሁኔታ ይለጠፍ።



ወደ ድርጅቱ ዋና መግቢያ በፊትለፊት በር መሆን አለበት፤ ወደ ኋላ በር ወይንም ሌሎች የመግቢያ በሮችን ሰዉ እንዳይደርስ ይገድቡ። መግባት የሚቻልበት በር የፊትለፊት በር ካልሆነ መግባት የሚቻልበትን መግቢያ ይፍቀዱ።



በሥራዉ ቦታ ጠቅላላ የንጽህና ገቢሮችን ይለጥፉ፤ ለ20 ሴከንዶች እጅ መታጠብ፤ የእጅ ሳኒታይዘር መጠቀም፣ ሌሎች የእጅ ማጽጃ ዘዴዎች ከሌሉ ላንድ ግዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚዉሉ ጓንቶችን መጠቀም።

## የደንበኞች ጤናና ደህንነት

ተቋሞ ዉስጥ በተለያዩ ቦታዎች በብዙ ቋንቋዎች ወቅታዊ የሆነ የማህበረሰብ ጤና መመሪያ እንዲታይ ያስቀምጡ። በነጻ ከ www.kingcounty.gov/covid ሊወርዱ የሚችሉ ከ30 በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች የሲያትልና ኪንግ ካዉንቲ ማህበረሰብ ጤና ፖስተሮች ይገኛሉ።



ደንበኞች የዉል ስምምነት ና የመልሶ መክፈት መርሖች ቁርጠኝነት መተዋቸዉን ወደ ተቋሙ ከመግባታቸዉ በፊት መፈረም አላባቸዉ፤ የስልጠና ደንብ ልብስ ወደ ተቋሙ ሲመጠ መለበስና ደንበኞች ያራሳቸዉን ፎጣ ማምጣት አለባቸዉ የፎጣ አገልግሎት ስለማይፈቀድ።



የቴኒስ ተጨዋቾች የራሳቸዉን ኳስ ማምጣት አለባቸዉ።




ደንበኞች በሽታዉ ከተገኘባቸዉ፣ አሁንም ተጋልጠዉ እያገገሙ ከሆነ ወይንም የCOVID-19 ምልክት እየታየባቸዉ ከሆነ መግባት እንደማችሉ የሚያስገነዝብ ምልክት መግቢያ ላይ ያስቀምጡ።



በኦንላይን ወይንም በስልክ ቦታ የማስያዝና የቅድመ ክፍያ አማራጮች ይኑሮት።



መጸዳጃ ክፍሎች፣ በብዛት ጥቅም ላይ የሚዉሉ ሥፍራዎችን፣ ና መሣሪያዎችን በተደጋጋሚ ያጽዱና ሳኒታይዝ ያርጉ (ጀርም ያስወግዱ)።



ሶፍት፣ የእጅ ሳኒታይዘር፣ ና የቆሻሻ መጠያ ተቋሙ ዉስጥ በየቦታዉ የተለያዩ ቁመትና ችሎታ ያላቸዉ ሰዎች ሁሉ ከሚደርሱበት ቦታዎች ያስቀምጡ። የቆሻሻ መጠያዎች የመዳዳዣ መንገዶች አለመዝጋታቸዉን ያረጋግጡ።



ደንበኞች ያራሳቸዉን የዉሃ ጠርሙዞችን ማምጣት አለባቸዉ፤ የዉሃ ምንጮች የዉሃ ጠርሙዞችን ለመሙላት ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸዉ።



አሰልጣኞች ከያንዳንዱ ክፍለ ግዜ በፊት እጃቸዉን መታጠብና የእጅ ሳኒታይዘር መጠቀም አለባቸዉ።



ሲቻል መስኮቶችን፣ በሮችን  በመክፈት ና/ወይንም ማራገብያ (ማቀዝቀዣ) በመጠቀም የአየር ዝዉዉርን ይጨምሩ።



ግንኙነት ያለዎትን ሰዎች ክትትልን ለማቀናጀት እንዲረዱ በጎ ፈቃደኛ የሆኑ ደንበኞች ዝርዝር ለማስቀመጥ ያስቡ። ዝርዝሩ ማካተት ያለበት ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ ና ድርጅቱን የጎበኙበት ቀን።

## ስለ ትብብርዎ እናመሰግናለን!